## ኢሕአፓና ኢሕአፓዎች፡፡ የዶክቶሩ እንቆቅልሽ፤ የምንሽር ምሬት እና የፕሮፌሰሩ ቅሌት

አቦ አራዳ አባ ሻውል

ግንቦት ፭ ቀን ፪ሺህ፯ ዓ.ም(ግንቦት 5 ቀን 2007 ዓ.ም)

በኢሕአፓና በኢሕአፓዎች መካከል የነበረውና ያለው ልዩነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያገረሸ አንደሄደ የአደባባይ ምስጢር እየሆነ መጥተዋል፡፡ ምክንያቱም ጉዳዩ ቀላልና ውስብስብ ስለሆነ ነው፡፡ ቀላል የሆነበት ምክንያት በአባሎቹ፤ በተባባሪ አባሎቹና በደጋፊዎች የሚታረቅ ቅራኔ ስለሆነ ቀለል ያደርገዋልና ነው፡፡ ይህ ማለት ድርጅቱ ኢሕአፓ የተገነባውና የሚያገለግለው ዓላማ ለሁሉም ኤትዮጵያውያን ስለሆነና መልካም ግንዛቤና ፍቅር ስለ አስተማረ ነው፡፡ የድርጅቱ ዓላማና አካሄድ ብሎም መመዘኛው ከአባሎቹ ሁኔታና ፍላጎት ስለ ማይለይ ነበር፡፡ ታሪካቸውም አንድና አንድ ነው፡፡ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ዴሞክራሲያ በኢትዮጵያ ለማስፈን ነበር/ነውም፡፡ ለዚህ ለተቀደሰ ዓላማ ድርጅቱ እስከ አሁን በተለያየ መንገድ ብዙ መስዋዕት እየከፈለና እያስከፈለ ይገኛል፡፡

ድርጅቱ ለምን መስዋዕት ያስከፍላል ለምን ራሱ አይከፍልም ሊባል ይቻላል? ድርጅቱ ግን ግዑዝ ስለሆነ በቀጥታ መስዋዕት ሊከፍል አይቻለውምና ነው፡፡ ነገሩ ለማብራራት ያህል የኢሕአፓ ድርጅት ተቋቋሚዊ ወይም institutional ስለሆነ ነው፡፡ በካፒታሊት አገር ለምትኖሩ ደግሞ እንደ ኮርፖረሽናዊ ፓርትነሺፕ ያለው ግንኙነት መሆኑ ነው፡፡እንደሚታወቀው በኢትዩጵያ ብዙ ብዙ አገራዊ ተቓሞች እንደ ቤተ-ክርስቲን፤ ቤተ-ሰብ፤ ማኅበረ-ሰብ፤ አፈርሳታ፤ ዕቁብ፤ ቄስ ትምሕረት ቤት ወዘተርፈ ነበሩ አሁንም አሉ፡፡ ነገር ግን የፖለቲካ ወይም ሥርዓተ-አሠተዳደር (ተቋም) ስለፈረሰ ኢሕአፓ ወራሽ ማን ሊሆን ይገባል ለሚለው ጥያቄ ለመመለስ እሰከ አሁኑ ሰዓት በትግል ላይ ይገኛል፡፡ ማንም ያላደረገውን ኢሕአፓ (ኤትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ) ብሎ ሥም አወጣ፡፡ ቋሚ institution ፈጠረ ማለት ነው፡፡ ይኸንን እንደ ኃጢአት ተቆጥሮ እነሆ በተቃዊሞዎቹ በኩል ታሪክ ለማጉደፍና አገርና ሕዝብ እንዳይበለጽግና እንዳያድግ በየጊዜው ሕዝብን ለማተራመስ ሩጫ ተይዘዋል፡፡

ከላይ እንደገለጥኩት ድርጅቱን ለማጥቃት ስለ ማይቻላቸው ተቃዊሞች በሆነ ባልሆነ ምክንያት የኢሕአፓ አባሎችን፤ ደጋፊዎቻውና ተባባሪዎቻቸውን ለማጥቃትም ሆነ ለማጥቆር ይራራጣሉ፡፡ ትግሉ ግን ይቀጥላል እነሱም ጭሆታቸውን ይቀጥሉ፡፡

እነሱ እነማን ናቸው? ብዙ ጊዜ ለመጻፍ የምሞክረው የመፍትሄ ሐሳብ ለመለገስ ነበር/ነውም፡፡ በእኔ ዕይታ እነሱ የምላቸው የድርጅቱን ዓላማና መንገዱ የማያውቁ፤ ያልተገነዘቡ የሚያውቁተን መሣሪያ ሁነው የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ በዚች ጽሁፌ ግን ሦስት ሰዎች የማዕርግ ሥማቸው ዶክተር፤ ምንሽርና ፕሮፌሰር ተብለው ሲታወቁ ሦስቱም በኢሕአፓ የትግል መሠመር የተሰለፉ ስለ መሆናቸው ከራሣቸው አንደበት ሰምተነዋል፡ በድርጅቱ በኢሕአፓ የሥራ ክፍፍል እንጂ የሥልጣን ክፍፍል ስለ አልነበረና ስለሌለ ማዕርጋቸው ይሄ ነበር ብዬ ለመናገር አልችልም፡፡ ለጊዜው ሁሉም ጓድ ወይም ብጻይ ብለን እንጥራቸው፡፡

## የጋድ ዶክተር እንቆቅልሽ

ዶ/ር አያሌው መርጊያው ጉበና ስለ ኢሕአፓ እንቆቅልሽ መጽሐፍ መጻፋቻውን በኢትዮሚዲያ ድህረ ገፅ አበስረውናል፡፡ መጻፋቻው ባልከፋ ነበር፤ ነገር ግን እንደምሁርነታቸው የምሑርነት ሥራ የሠሩ አይመስልም፡፡ መጽሃፈቸው በገበያ ስላላገኘሁት ለማንበብ አልቻልኩምና ብዙ የምለው የለኝም፡፡ በዚህ መጣጥፌ ለማለት የፈለኩት ጉዳይ ግን አለ፡፡ ይኸውም አርዕስታቸው እንቆቅልሽ ስለሚል እንቆቅልሹን ለመፍታት መቸኮላቸው ነው፡፡ ከመቸኮላቸው በላይም ጥቅሶቻቸውን ያለ ቦታና ጊዜ ከማጎደሩ ውጭ እያላተሙ በስማ በለው መጥቀሳቸው ነው፡፡ ዋለልኝ እንዲህ አለ ብርሃነ መስቀል፤ ይርጋ ተሰማ እንደዚያ አለ ብሎ አሉባልታ ከማጣቀስ በላይ ሁሉንም በጅምላ የኢሕአፓ ሰዎች፤ የሜኤሶን ሰዎች ፤የኦኤልፍ ሰዎችና የደርግ ሰዎች በአንድ ዘምቢል በማጎራቸው ጽንሐተ ምሁር ሳይሆኑ ተራ ምሁር አድርጎቸዋል፡፡ ምሁር ማለት እኮ በእንገሊዘኛ ድኩተርና ባአገኙበት ማለቴ ነው CC (concept እና context) ሲያጣቅሱ በማንበቤ ነው፡፡

ለመሆኑ መቼ ነው ከኢሕአፓ ጋር የተዋወቁት? ለማለት የፈለግሁት ከድርጅቱ ዓላማና ፍፃሜ origin-destination (O-D ለማለት እንጂ ኢሕአፓዎች ለማለት አይደለምና ጥያቄን በጥንቃቄ ይመርምሩትና ከቻሉ መልስ ይስጡበት፡፡ Motivated ሁነው ነው ወይስ Inspired ሆነው ኢሕፓን የተቀላቀሉ ቀናነት ካሎዎት ይንገሩንና እንቆቀልሹን እንፈታዎታለን፡፡

በተረፈ እኔም መጽሐፎዎን ላንብብ እርስዎም መልስ ያዘጋጁ የጽንሐተ-ምሁር መልስ ማለቴ ነው እንጂ ከሰሙትና ካነበቡት ብቻ ከሆነ ላንግባባ እንችላለንና ነው፡፡ በጥናትና በምርምር ከሆነ እንቆቅልሹ ሳይፈታ አይቀርም፡፡ ኤትዮጵያ አያሌ ጽንሐተ-ምሁራን አላትና፡፡

## የጋድ ምንሽር ምሬት

የአቶ አሸናፊ አራጋው ጽሁፍ በአሲምባ ድህረ-ገፅ ወጥተዋል፡፡ ጓድ ምንሽርን በሚገባ አውቃቸው አሉ የሰፈሬ ሰው ናቸው፡፡ ከአሰርት ዓመታት በፊት "ተጠንቀቅ አማራ" ብለው ከመጻፋቸው በፊት ክፍሉ ታደሰ ስለማይሰጠኝ አንተ ጠይቅና የዋለልኝ መኮንን የመገንጠል ጸሑፍ አሰጠኝ ብለውኝ እኔ ዋናውን እሰጦት አለሁ በማለት ከጸሐፊው ወንድም ጋር አገናኝቻቸው ነበር፡፡ በዋለልኝ መኮንን ወንድም አገላለጥና አባባል የረኩ መሰለኝ፡፡

ይህነን ከላይ የምገልጠው አቶ አሸናፊ ዝም ብለው ያለ ምክንያት ወይም  ያለ መረጃ የሚጽፉ አልነበሩም ለማለት ያህል ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ታሪክ ጸሐፊዎች አለቁና ደንቆሮዎች(ምንም የመያውቁ) መጻፍ ጀመሩ ብለው በአሲምባ ድህረ-ገፅ ማስፈራቸው ምን ይሆን ብዬ አግኝቼ እጠይቀአቸው ነበር፡፡ የኔ ጥያቄ ለምድን ነው መረጃ ያልጠየቁኝ ወይስ መረጃ አገኝተው ነው ያልጠየቁኝ ብየ ነበር፡፡

የሳቸው መልስ ግን እንዲያውም አንተም በሚቀጥለው አይቀርልኽም ብለውኛል እንዳልጽፍ ማስፈራራቸው እንዳልሆነ ግን እርግጠኛ ነኝ ፡፡ አቶ አቸናፊ በጣም የተማረሩ ናቸው፡፡ ምክንያቱም የኢሕአፓ መዳረሻ -DESTINATION- ለማየት ይሻሉና፡፡ የተጀመረው የትግል ጉዞ መቃጠሪያ ያስፈልገዋልና ነው፡፡ ቅድሚያ የሚሰጠው ይኸው ነው ብለው ያምናሉ፡፡ መዳረሻ ያስጨብጡን ስላቸው የፀገየ ደብተራው ጉዳይ ነው ይላሉ፡፡ እንደገባኝ ኢሕአፓዎች በጦርነትም ሆነ በትግል ሲቆስሉም ሆነ ሲሰዉ፤ መንከባከብም ሆነ መቅበር ባሕላችን እና ግዴታችን ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ይኸንን ከማድረግ አልፈው ድርጅተ-ኢሕአፓ መዳራሻ ሳያዩና ሳያገናዝቡ መጽሐፍ ለመጻፍ ሲራራጡ ያውም እውነተኛ ታሪከ-ኢሕአፓ ያላገናዘበ ሲሆን አቶ አሸናፊ በጣም ያናድዳቸዋል፡፡

እኔም በበኩሌ ደራሲዎች ነን ብለው መጽሀፍ ከጻፉ ተቃውሞ የለኝም፡፡ መናገር መብታቸው እንደሆነ ሁሉ መጻፍም መብታቸው ነውና፡፡ ታዲያ ችግሩ የኢሕአፓዎች ግለ-ታሪክ ወይም ማስታወሻ በሚል ቢጽፉ አቶ አሸናፊ ችግር ያላቸው አይመስለኝም፡፡ ስለ ታሪከ-ኢሕአፓ መጻፍ እንኳን ለአቶ አሸናፊ ቀርቶ ለኔም አይጥመኝም፡፡ ምክንያቱም እሳቸው ገና ትኩስ ኃይል Activist ሲሆኑ እኔ ደግሞ ተካላካይ ኃይል Advocate ነኝ እላለሁና ነው፡፡

የሚከተሉት የታሪክ ምሁር ሰሞኑን ስለ ኢሕአፓነታቸው ያሉትን እንመልከትና ዕውነት የሠለጠኑ የታሪክ ጸሐፊዎች አሉን ብለን ለመጠየቅና ለማማረር እንገዳዳለን፡፡ የፕሮፈሰሩ የትግልና የዓላማ ኢሕአፓዊ ታሪክ ነው ብለው ሲግልጡ እኔም እንደ አሸናፊ ከአክሱም መስቀል  ይልቅ ምንሽር መያዝን ተመኘሁ፡፡

## የብጻይ ፕሮፈሰር ቅሌት

ፕሮፈሰር ገብሩ ታረቀ ፕሮፈሰር በመሆናቸው ብዙ አንባቢ የሆነ ሰው ያውቃቸዋል፡፡ አሁን ድግሞ አድማጮች ሁሉ እንዲያወቀቸው እያደረጉ ናቸው፡፡ በድርጅታዊ ታሪከ-ኢሕአፓ ወይንም በ(አክቲቭዚም) ተሳትፎዋቸው ጉዳዩን ቢያስረዱን መልካም ነበር? እሱ እሳቸው ቢያስረዱን ይሻላል ልዩነቱን ካወቁ ማለቴ ነው፡፡ የልባችንና የአዕምሮዋችን ውሕደት ተረኩልን እንደማለት እንቆጥረዋለንና ነው፡፡ የፕሮፈሰር ገብሩ ኢሕአፓዊ ተሳትፎዋቸው በአያሌ ፌስ-ቡክ ተለጥፈዋል፡፡

ከፕሮፈሰሩ ጋር የብዙ ዘመን ትውውቅ ነበረን፡፡ በአብዮት ጉዞ ግና አብረን መጋዛች ያጠራጥራል፡፡ ለእኔ የኢትዮጵያ አብዮት ማለት የደርግ አማካሪ ምሁራኖች ከሶቪየት ኅብረት የቀዱትን ንድፈ-ሐሳብ ፤ የወያኔ መሪዎች የተከተሉትን የአልባኒያ ቀኖና ወይንም የሕዝባዊ ግንባር የማኦ ዘዶንግ ራሥህን እርሳ መፎከር እንዳይደለ እንዲታወቅልኝ እፈልጋለሁ፡፡

የኢትዮጵያ አብዮት ማለት ኢትዮጵያ ላይ የነበረና አሁንም ያለ አብዮት ነው፡፡ ከተፈለገ ሁለት መጣጥፎች በሚከተለው በእንግሊዘኛ የተጻፈ ማንበብ ይቻላል፡፡ [www.http://ethiolion.com/oboaradashwl](www.http://ethiolion.com/oboaradashwl)

ፕሮፈሰር ገብሩ ከአክሱም መወለዳቸው አሳውቀውናል፡፡ እንግዲያውስ የኢትዮጵያ ታሪክ የሚጀምረው ከእርስዎ የተወለዱበት መንደር  መሆኑን እንዴት ረሱት? የተማሩትም ታሪክ ነው ተግባሩ ግና የት አለ፡፡ እርስዎ የሚነግሩን ያለ የቪየትናም፤የአሜሪካ የጥቁር እና የኢራን ትግል ወዘተርፈ ነው፡፡ የኢትዮጵያ አብዮት በሚመለከት አሁንም ከውጭ ለመዘከር USUNA; Combat Challenge እያሉ ቢያመሳክሩ ተቀባይነት አለውን? በበኩሌ አይመስለኝም፡፡ እርስዎና እሸቱ ጮሌ ከሌሎች የዩኒቨረሲቴ መምሕራኖች በተለየ የተራማጅ መጽሕፍት ስለአነበባችሁ ከደርግ አብዮትና ብሔረተኞቹ የተለየ አመለካከት ለዛውም ሣሙኤል ዓለማየሁ የተሳተፈበት ላብአደራዊ አብዮት አባሎች ነበርን ስትሉ ታሪክ አይፈርድም ትላላችሁ?

ይልቁንስ ልጠቁሞት የኢትዮጵያ ታሪክ ለመጻፍ ከፈለጉ አክሱም-አንኮበር-ዝግብ ብለው ይጀምሩ እርስዎ የተሳተፉበት የአብዮት ታሪክ ደግሞ አሲምባ-ጠለምት-መርካቶ ብለው አብዮተ-ኢትዮጵያዊ ብለው ይመራመሩ፡፡ ምስጢሩን ያገኙታል፡፡

በተረፈ የኢትዮጵያ አብዮት በሚል ታሪክ ብዙም አልጣመኝም በተለይም የኢትዮጵያውያ መከላከሊያ ሚኒስተር አክሰስ ሙሉ በሙሉ በማግኘትዎ፡፡ ነገር ነገርን ያነሰዋልና በበጋ በመካለከያ ሚኒስተር ሥራ አግኝቼ ሥሰራ፤ ስራዬ የመሣሪያዎች ኢንቨንቶሪ

ማድረግ ነበር፡፡ ታዲያ አንድ ቀን አለቃየን አስጠርቸ አንድ ጥያቄ ጠየቀኩት እሱም የመዘገብኩዋቸው መሣሪየያቹ የት እንደሚገኙ ነበር፡፡ አለቃየ ከዛ በኋላ አልተመለሰም እኔም ሳመሩን ሙሉ ደሞዜን እየተቀበልኩ አሳለፍኩት፡፡ ነገሩ ቀላል ኖረዋል፡፡ ከፍተኛ ሚሥጢር ስለነበረ ነው፡፡ በምን ምክንያት ለእርስዎ ክፍት እንደሆነ ግን ለብዙ ሰዎች አርዕስት ሆኖ ነበር፡፡ እርሶዎ ም አልጠየቁም ይሆናል ለምን የሚለው ጥያቄ ብዙም ሰው አይጋፈጠውምና ነው፡፡

ሌላው ጉዳይ ደግሞ ከዚህ ቀደም የኢሕአፓ ጉዳይ እንደ ያልለየለት፤ ያልተብራራ፤ ግራ የሚያጋባ ወዘተ በማለት በእንግሊዘኛ ጽሁፍዎ aberration በሚል እንዳስቀመጡት ትዝ ይለኛል፡፡ አሁንስ ተገለጠሎዎት ማለት ነው፣ ማለቴ ሁለት የኢሕአፓ ጓዶችዎ በሕይወት ስለሌሉ ነው አሁን መናገር አለብኝ ነው ጉዳዩ ስላልገባኝ ነው፡፡ ቢያብራሩልኝ ደስ ይለኛል፡፡

የወደቁትን ብጾት ወይም ሰዎች በአንድ ወቅት በዚች ዓለም መኖራቸው ለመዘከር አይደለም ታሪክ ማለት እንደ እኔ ያልተማረ የሚያስበው፤ ይህማ የሥጋ ዘመዶቻቸውና እግዚአብሔር ያቁታል፡፡ ለእኛ መሆን ያለበት እነዛ ሰዎች ምን ሠርተው አለፉ ለመጪው ትውልድስ ምን ትተው አለፉ ነው፡፡ የምሁር ድርሻዎ ብቻ ሳይሆን የሚፈለገው የጽንነተ ምሑር ድርሻዎን ለሚቀጥለው ትውልድ እንዲያስረክቡ ነበር፡፡ ፅንነተ ምሑር ማለት በግዕዝ ትንሽ እንደ የርስዎ እንግሊዘኛ aberration ስለሚጠጥር concept-theory-application በንድነት ለማለት ነው፡፡ ቲዎሪና ተግባር በሚገባ እንደሚያውቁ ይገባኛል ሆኖም በጽንሱ እጠራጠራለሁ፡፡

## መደምደሚያ

አቶ አሸናፊ መሮዋቸው በትግል ጠሐፊ ጓዶቻቸው ላይ የከረረ ስድብ አዘል ወቀሳ በመፃፍ ስሜታቸውና ምሬታቸውን ገልጠውልናል፡፡ የሜዳ ታጋይ ስለነበሩ የሜዳ ትግል ደግሞ ስለ አላማረ በሜዴኞች ላይ በአጠቃላይ አወገዙዋቸው፡፡ የሜዳ ጉዳይ ግን ብዙ ታሪክ ስለአለው ማለትም ምን ማለት ነው፤ ለምንድን ነው፤ ማነው የታጠቀው፤ ዓላማውና ግቡ የት ነው፤ እነማን ትተውን ሄዱ ብቻ ሳይሆን እነማን ከዱን የመሳሰሉት ሲተረኩ ነው እንጂ እንዲሁ ወያኔ ብቻ በሚያናፍሰው ተዋጊና አለተዋጊ፤ ተሸናፊና አሸናፊ እያሉ በሚዋሹት ደርግ ያደርገው የነበረው ቀረርቶ በምንም መልኩ አይሻልም፡፡

ዶ/ር ጉበና በሜዳ ያገኙትን ልምድና ሥልጠና በመሠረቱ ሳያላምጡ ወደ ንድፈ-ሐሳብ ሄደው ያለፉበትን ለማወቅ ሲጥሩ ዕውነትም ቅዠት እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም፡፡ ሰከን ብለው ሁለቱን ፅንሰ-ሐስብና ንደፈ-ሐሳብ ቢያቀናብሩ እንዴት ያለ ተግባራዊና ፍሬያማ ውጤት ያስገኙ ነበር፡፡ አሁንም ተስፋ ሳይቆርጡ ጥናቱን ያካሂዱ፡፡ ኢሕአፓና ኢሕአፓዎችን ያስታርቁ፡፡

ፕሮፌሰር ገብሩ ብዙ ተጉዘዋል፤ ብዙ ነገር አይተዋል፡፡ ሆኖም ትንሽ ዞር ብለው ወደ ውስጥዎ ለማየት አልሞከሩም፡፡ ፈላስፋው ዘርዐ ያቆብና ቅዱስ ያሬድ እነማን ነበሩ፤ ለምንስ እና እንዴትስ ኢትዮጵያን ይጠቅማሉ ብለው አልተመራመሩም፡፡ እርሶ ሊነግሩን የሚፈልጉት ንጉሥ ዘርዐ ያቆብ እና ንጉሥ ፋሲል፤ አለበለዚያ ደግሞ ቴዎድሮስ እና ዮሓንስ የመሳሰሉትን ነው፡፡የፖለቲካ ጎድናቸውን ነው፤ እርስዎ ደግሞ የአብዮት እና የአመፅ ታሪኮችን ነው፡፡ ታዲያ እንዴት ማቀናበር አቃቶዎት፡፡ ኮከብዎ ነው እንዳልል የመሪነት ኮከብና የሥነ-ምግባር ኮከቦች አይጋጩም ነበር፡፡ ለማነኛውም ብርታቱን ይስጦትና ኢሕአፓና ኢሕአፓዎችን ያስታርቁ እርስዎም ከቅሌት ይድናሉና፡፡

For comments and critics

oboaradashawl@gmail.com